የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር- OFAG.ቶ03.3/1/38
ቀን- 15/07/2015

ለክብርት ዶ/ር ፍፁም አሰፋ

የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር

ለክቡር ዶ/ር በከር ሻሌ

የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎትን የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ይመለከታል፤</u>

የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 30 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 13 ገጽ የሂሣብ ሪፖርቶች በድምሩ 43 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አበራ ታደሰ
የፌዴራል ም/ዋና ኦዲተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ

ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት /2015

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የተመደበለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና ሪፖርቶችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች (Basic of Audit Opinion)፣

የአገልግሎቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ፣ ደንብና መመሪያ የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. **በተጠቃለለው የመደበኛ የሂሳብ ሪፖርት ላይ ያለአግባብ የተመዘገበ የፕሮጀክት ሂሳብ በተመለከተ፣**

   የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሶስት የመንግስት ሂሳብ ሪፖርት ይዘት እና ማቅረቢያ አንቀጽ 11 ተራ ቁጥር 1 መሰረት የመንግስት መ/ቤቶች ከትሬዠሪ ምንጭ፣ ከብድርና እርዳታ የሚያገኙትን ሂሳብ አጠቃቀም ሪፖርት በየወሩ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ አገልግሎቱ፣-

   - ለ23 ቅ/ጽ/ቤቶች ለመደበኛ እና ለፕሮጀክት ሂሳብ ገንዘብ ገቢና ወጪ ማድረጊያ የተከፈተው አንድ የንግድ የባንክ ሂሳብ ቁጥር በመሆኑ በበጀት ዓመት መጨረሻ ሰኔ 30/2014 ዓ.ም በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በባንክ ያለ ጥሬ ገንዘብ (4103) ከወጪ ቀሪ በድምሩ ብር 73,924.69 የሚታይ ሲሆን ገንዘቡ ለመንግስት ፈሰስ መሆኑ ቢረጋገጥም ሂሳቡ የመደበኛው ወይም የፕሮጀክት ሂሳብ ለመሆኑ መለየት የማያስችል መሆኑ፣
   - በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የባንክ ሂሳብ ሪፖርት እና የባንክ መግለጫው (statement) ከባንክ ማስታረቂያው ጋር የመደበኛ እና የፕሮጀክት ሂሳቦች ለየብቻቸው ተሰርቶ ሪፖርት መደረግ ሲገባው ቅ/ጽ/ቤቶቹ በመደበኛ የሂሳብ ሪፖርት አካተው የሚልኩ እና በዋናው መ/ቤትም የመደበኛ እና የፕሮጀክት የባንክ ሂሳብ ሳይለይ በተጠቃለለው የመደበኛ የሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ተካቶ የተመዘገበና ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣
   - በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በየወሩ እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30/2014ዓ.ም) በ4101 የሂሳብ መደብ በገ/ያዥ እጅ ያለው ጥሬ ገንዘብም ሆነ ሰነድ ቆጠራ ሲደረግ የፕሮጀክት እና የመደበኛ ሂሳብ ለየብቻቸው ተለይቶ ቆጠራ የማይደረግ እና ከሌጀር ሚዛኑ ጋር የማይመዛዘን መሆኑ፣

- በሰኔ 30/2014 በጀት ዓመት ከወጪ ቀሪ ከሚያሳየው በ22 ቅ/ጽ/ቤቶች በሂሳብ መደብ 4211 በድምሩ ብር 2,174,695.04 እንዲሁም በ07 ቅ/ጽ/ቤቶች በሂሳብ መደብ 4274 በድምሩ ብር 3,929,772.72 የመደበኛው ወይም የፕሮጀክት ተሰብሳቢ ሂሳቦች ሳይለዩ ከየቅርጫፍ ጽ/ቤቶች በመደበኛ ሂሳብ ሪፖርት ተካተው የሚላኩ እና በዋናው መ/ቤት በተጠቃለለው የመደበኛ የሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ተካተው የተመዘገቡና ሪፖርት የተደረገ በመሆኑ የመደበኛ ሂሳብ ሪፖርት ከፍ ብሎ እና የፕሮጀክት ሂሳብ ዝቅ ብሎ የሚታይ መሆኑ፤
- በየቅ/ጽ/ቤቶቹ ከተለያዩ ከሶስተኛ ወገን የሚመጡ የእርዳታ ወይም የፕሮጀክት ሂሳቦች የፕሮጀክት ሂሳብ ሪፖርት ራሱን ችሎ ያልተዘጋጀለት በመሆኑ የፕሮጀክት ሂሳቦች በመደበኛ የሂሳብ ሪፖርት ተካተው የሚቀርቡ እና በዋናው መ/ቤትም በተጠቃለለው የመደበኛ የሂሳብ ሪፖርት ከተለያዩ የፕሮጀክት ሂሳቦች ለባለመብቱ ያልተከፈሉ ተከፋይ ሂሳቦች (በሂሳብ መደብ 5028) በ2013 በጀት ዓመት የዞረ ሚዛን በድምሩ ብር 5,977,577.06 እንዲሁም በ2014 በጀት ዓመት ከወጪ ቀሪ በድምሩ ብር 767,939.87 በአጠቃላይ በድምሩ ብር 6,745,516.93 በአገልግሎቱ በተጠቃለለው የመደበኛ የሂሳብ ሪፖርት ተካተው ሪፖርት የተደረጉ በመሆኑ የመደበኛ ሂሳብ ሪፖርት ያለአግባብ ከፍ ብሎ እና የፕሮጀክት ሂሳብ ዝቅ ብሎ እንዲታይ ያደረገው መሆኑ፤

በአጠቃላይ የቅ/ጽ/ቤቶች የፕሮጀክት ሂሳብ ውስጥ የባንክ ሂሳብ፣ የተሰብሳቢ ሂሳብና የተከፋይ ሂሳብ ከመደበኛ ሂሳብ ጋር ተካቶ ለዋናው መ/ቤት ሪፖርት የሚደረግ ሲሆን ዋናው መ/ቤት የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርት ሲያዘጋጅ የመደበኛውንና የፕሮጀክት ሂሳቡን ሳይለይ የሚመዘገብና ሪፖርት የሚያደረግ በመሆኑ የመደበኛም ሆነ የፕሮጀክት ሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

2. <u>ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ እያለ ከፍተኛ ዋጋ ያቀረበ ድርጅት እንዲያሸንፍ የተደረገበት ግዥን በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 6 ተቀራራቢ የጥራት ደረጃ ያላቸዉና መ/ቤቱ የሚፈለገዉን የጥራት ደረጃ የሚያሟሉ አቅርቦቶችን በማወዳደር ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበዉን ተጫራች አሸናፊ አድርጎ መምረጥ እንደሚያስፈልግ እንዲሁም በዚሁ መመሪያ ክፍል አንድ አንቀጽ 4 ፊደል ሀ በግዥ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ማስገኘት እንደሚገባ ይህም ማለት

ቁጠባን፣ የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ እንዳለበት መመሪያው ይገልፃል፡፡

ይሁን እንጂ በአገልግሎት መ/ቤቱ በአርባ ምንጭ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትበቀን 12/09/2014 በባንክ የወጪ ማስማስከሪያ ቁጥር 523671 ለስልጠና የአዳራሽ እና የሻይ ቡና መስተንግዶ (Refreshment) አገልግሎት ግዥ፣ በቀን 25/06/2014 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 447576 የመኪና እቃ ግዥ እና በወላይታ ሶዶ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቀን 03/09/2014 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 0151920 የደንብ ልብስ (ውስጥ ልብስ) እንዲሁም በቀን 30/10/2014 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 601773 የደንብ ልብስ (ቱታ) ስፌት ግዥዎች ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ ድርጅቶች እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ያቀረቡ ድርጅቶች ግዥውን እንዲያሸንፉና ክፍያ እንዲፈጸም በመደረጉ በድምሩ ብር 147,468.37 መንግስት ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 2 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የሂሣብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበው ገቢ የተፈጸመው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

<u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች (Emphasise Matters)</u>

1. <u>የፕሮጀክት ስራቸው ተጠናቆ የባንክ ሂሳባቸው ያልተዘጋ የፕሮጀክት ሂሳብ በተመለከተ፣</u>

   የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 20 ተራ ቁጥር 1 እና 2 ማንኛውም መ/ቤት በስሙ የተከፈተለትን የባንክ ሂሳብ አገልግሎት ሲያጠናቅቅ ወይም መ/ቤቱ ከሌላ ጋር እንዲዋሃድ ሲደረግ ወይም ሲፈርስ ወዲያውኑ በውስጡ የሚገኝ ገንዘብ ወዴት እንደሚተላለፍ በመግለጽ የባንክ

ሂሳቡ እንዲዘጋ ለሚኒስቴሩ በጽሑፍ ማሳወቅ እንዳለበት እንዲሁም ለብር ሂሳብ ማንቀሳቀሻነት የተከፈተው የባንክ ሂሳብ ሳይንቀሳቀስ ለ12(አስራ ሁለት) ወርና ከዚያ በላይ ከቆየ ሚኒስቴሩ የባንክ ሂሳቡን ሊዘጋ እንደሚችልና መ/ቤቱም አሳማኝ ማብራሪያ ከሰጠበት የባንክ ሂሳቡ በቀድሞ ሁኔታ እንዲቀሳቀስ እንደሚደረግ ይገልፃል፡፡ይሁን እንጂ በአገልግሎቱ ከየተለያዩ ለጋሽ አገሮችና ድርጅቶች በእርዳታ የመጡ የፕሮጀክት ሂሳቦች እንቅስቃሴ የሌላቸው ወይም የተዘጉ ሂሳቦች በሳጥን እና በባንክ ያለ ጥሬ ገንዘብን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በ9 የተለያዩ ፕሮጀክት ሂሳቦች ፕሮጀክቶቹ ስራቸውን አጠናቀው ሳለ በሳጥን ያለ ጥሬ ገንዘብ (4101) በሌጀር ሚዛን መሰረት በድምሩ ብር 57,335.41 የሚታይ መሆኑ፣
- በሶስት(3) የተለያዩ የፕሮጀክት ሂሳቦች በብሔራዊ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000000985728 ብር 9,205.39፣ በብሔራዊ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000000985612 ብር 21,178.02 እና በብሔራዊ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000000985857 ብር 932.79 በድምሩ ብር 31,316.20 በባንክ ያለ ጥሬ ገንዘብ የፕሮጀክቶቹ ስራ ተጠናቀው ሳለ ከስምንት እስከ አስር አመት የባንክ የሂሳብ እንቅስቃሴያቸው ሳይንቀሳቀስ የቆየ እና የባንክ ሂሳብ ቁጥራቸው ያልተዘጋ መሆኑ፣
- በሁለት(2) የተለያዩ የፕሮጀክት ሂሳቦች በብሔራዊ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 0100451040044 ብር 608,670.44 እና ብር 5,417,301.39 በድምሩ ብር 6,025,971.83 በባንክ ያለ ጥሬ ገንዘብ የፕሮጀክቶቹ ስራ ተጠናቀው ሳለ ከአንድ ዓመት በላይ የባንክ የሂሳብ እንቅስቃሴው ሳይንቀሳቀስ የቆየ እና በዚሁ የባንክ ውስጥ ሌሎች እንቅስቃሴ ያላቸው ፕሮጀክት ሂሳቦች ቢኖሩም አገልግሎቱ ገንዘቡ ወዴት እንደሚተላለፍ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በጹሑፍ ያላሳወቀ መሆኑ፣
- በብሔራዊ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 0100451040045 በ13 የተለያዩ ፕሮጀክት ሂሳቦች ከስድስት ዓመት በላይ በድምሩ ብር 6,067,996.10፣ በ6 የተለያዩ ፕሮጀክት ሂሳቦች ከሶስት ዓመት በላይ በድምሩ ብር 10,985,141.20 እና በ4 የተለያዩ ፕሮጀክት ሂሳቦች በድምሩ ብር 9,217,689.08 አንድ ዓመት የሆነው በዚሁ የባንክ ሂሳብ ቁጥር በድምሩ ብር 26,270,826.38 በባንክ ያለ ጥሬ ገንዘብ የፕሮጀክቶቹ ስራ ተጠናቀው ሳለ በሌጀር ሚዛን መሰረት የባንክ የሂሳብ እንቅስቃሴው ሳይንቀሳቀስ የቆየ እና በዚሁ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ሌሎች እንቅስቃሴ ያላቸው

ፕሮጀክት ሂሳቦች ቢኖሩ አገልግሎቱ ገንዘቡ ወዴት እንደሚተላለፍ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በጹሑፍ ያላሳወቀ መሆኑ፣

በአጠቃላይ 28 የተለያዩ ፕሮጀክቶች ስራቸው ተጠናቆ ሳለ በድምሩ ብር 32,328,114.41 በሶስት(3) የተለያዩ ፕሮጀክቶች እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ችለው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ያላቸው ከ8 ዓመት በላይ የባንክ ሂሳብ እንቅስቃሴያቸው ሳይንቀሳቀስ የቆየ እና የባንኩ ሂሳብ ቁጥራቸው ያልተዘጉ መሆኑ፣ ሁለት(2) የተለያዩ የፕሮጀክት ሂሳቦች በአንድ የባንክ ሂሳብ ቁጥር እንዲሁም 23 የተለያዩ ፕሮጀክት ሂሳቦች በአንድ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ ከአንድ ዓመት እስከ ስድስት ዓመት ለፕሮጀክቶቹ ለብር ሂሳብ ማንቀሳቀሻነት የተከፈቱት የባንክ ሂሳቦች ሳይንቀሳቀሱ የቆዩ እና በእነዚህ ሁለት የብሔራዊ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ ሌሎች እንቅስቃሴ ያላቸው ፕሮጀክት ሂሳቦች ቢኖሩም አገልግሎቱ ገንዘቡ ወዴት እንደሚተላለፍ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በጹሑፍ በማሳወቅ ተገቢውን እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

2. ባልተለመደ የሂሳብ ምዝገባ የሚታይ የፕሮጀክት ሂሳብን በተመለከተ፣

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 ፊደል ለ እያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን (ዴቢት ወይም ክሬዲት) ጠብቆ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ፡-

- በዋናው መ/ቤት ከUNICEF ፕሮጀክት ሂሳብ የተቀጽላ ሌጀር ኮድ ወይም መለያ UNICEF በሂሳብ መደብ 4103 (በባንክ ያለ ጥሬ ገንዘብ) ብር 327,448.81፣
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በተከፋይ ሂሳብ በሂሳብ መደብ በ5028 (በመንግስት መ/ቤቶች መካከል ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች) በተለያዩ ተቀጽላ ሌጀር መደቦች ብር 3,125,780.77 እንዲሁም በ5054(ሌሎች የመያዣ ሂሳቦች በድምሩ ብር 150,851.10፣

በአጠቃላይ የባንክ ሂሳብ ብር 327,448.81፣ በሚታወቁበት የሂሳብ ሚዛን ዴቢት መመዝገብ ሲገባቸው ባልተለመደ የሂሳብ ምዝገባ ወይም ክሬዲት የተመዘገበ መሆኑ እና በድምሩ ብር 3,276,631.87 የተከፋይ ሂሳቦች በሚታወቁበት የሂሳብ ምዝገባ በክሬዲት መመዝገብ ሲገባቸው ባልተለመደ የሂሳብ ምዝገባ ወይም ዴቢት የተመዘገቡ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

3. <u>ባልተሟላ ማስረጃ የተፈፀመ ክፍያ እና በኮፒ የእቃ ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ፣ የተወራረደ ሂሳብን በተመለከተ፣</u>

የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ 4 እና አንቀፅ 9 መሰረት ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ወጪ ከመደረጉ በፊት የመንግስት መ/ቤቶች ክፍያ የሚፈፀምባቸው ወጪዎች አግባብነት ያለውና እንዲሁም ለሚፈጽሟቸው ክፍያዎች ተገቢ የሆነ ማስረጃ ከወጪ ሰነድ ጋር አብሮ ተያይዞ መቅረብ ሲችል ብቻ ነው በማለት ይገልጻል፡፡ እንዲሁም በዚሁ መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀጽ 9/7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ዋናው ደረሰኝ መቅረብ እንዳለበት መመሪያው ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት ስለመስራቱ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በአርባ ምንጭ ቅ/ጽ/ቤት በሂሳብ መደብ 6271 በድምሩ ብር 184,649.19 የተሳታፊዎች የሰዓት መቆጣጠሪያ(attendance) ባልቀረበበት ሁኔታ በቂ ማስረጃ ሳይያያዝ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- በሶዶ ቅ/ጽ/ቤት በቀን 03/09/2014 በሒሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 0151920 ብር 30,156.57 ለቅ/ጽ/ቤቱ የደንብ ልብስ (ፓሊስተር ጨርቅ ልብስ)፤ ካኪ ፓሊስተር፤የዉስጥ ልብስ ጨርቅ፤ቀሚስ ባለ አበባ) ከያህዌነወሲ ልብስ ቤት ግዥ የፈጸመ ሲሆን የተገዛው እቃ ወደ ቅ/ጽ/ቤቱ ገቢ ስለመደረጉ የሚያረጋግጥ ኮፒ እንጂ ዋናው (original) የንብረት ገቢ ደረሰኝ ከወጪ ሰነዱ ጋር ያልቀረበ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

4. <u>ያለሂሳብ መደቡ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም በክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መ/ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣው ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይተው በተሰጡዋቸው የበጀት መለያ መደቦች ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል:: በዚሁ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፡-በአዳማ ብር 36,895.92 እና በሃዋሳ ብር 4,621.67 በድምሩ ብር 41,517.59 ያለ ሂሳብ አርዕስቱ በሌላ የሂሳብ መደብ/አርዕስት የተመዘገበ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

5. ከፕሮጀክቱ አላማ እና ተግባር ውጪ የተፈጸመ ክፍያን በተመለከተ፣

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001ዓ.ም አንቀጽ 2/16 ፊደል መ የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ምንጮች ተብለው ከተገለጹት ውስጥ አንዱ ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት በባለሁለት ወይም በባለብዙ ወገን ስምምነት ወይም በእርዳታ የሚገኘው ገንዘብ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት አገልግሎት መ/ቤቱ ከሶስተኛ ወገን የመጡ የእርዳታ ገንዘብ ወይም ፕሮጀክት ሂሳብ ለታለመለት አላማ ለመዋሉ ኦዲት ሲደረግ፡-

በዋናው መ/ቤት በተለያዩ የክልል ወረዳዎች ላይ የአረንጓዴ ልማት ንቅናቄ የችግኝ ተከላ ለሄዱ ሰራተኞች በሸዋሮቢት ከተማ ለሁለት ቀን የመኪና ኪራይ አገልግሎት ክፍያ በቀን 05/12/2013 ዓ.ም በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኝ ቁጥር 691058 ብር 50,400.00 ለፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት የተከፈለ መሆኑ እንዲሁም በዚሁ ከተማ ለሚገኘው የደጃዝማች ተሰማ/ዙጢ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ለአምስት የመማሪያ ክፍሎች እድሳት በሚል በቀን 28/11/2013 ዓ.ም በባንክ የወጪ ማስመስከሪ ቁጥር 691493 ብር 100,000.00 በትምህርት ቤቱ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000028764239 ገቢ የተደረገ መሆኑ፣

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 150,400.00 ከPSNP 4 ፕሮጀክት ክፍያው ሲፈጸም ፕሮጀክቱ ከመጣበት ዓላማ እና ተግባር ውጪ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

6. በሂሳብ መደብ 4274 (ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦች) በተለያዩ ፕሮጀክት ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር የሚታይ የመክፈቻ ሂሳብ (Opening Balance) በተመለከተ

በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት

- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 563359 በቀን 30/10/2012 ተቀጽላ ሌጀር ኮድ 0010 ብር 49,983.64፣ በተቀጽላ ሌጀር ኮድ s001 ብር 32,887.17 እና በተቀጽላ ሌጀር ኮድ sc02 ብር 23,444.68 በድምሩ ብር 106,315.49 የፕሮጀክት ሂሳብ ከተላከላቸው በላይ ለተጠቀሙት በሚል በተሰብሳቢ ተመዝግቦ የሚታይ መሆኑ፣

- በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 324043 በቀን 28/02/2011 ዓ.ም በተቀጽላ ሌጀር ኮድ pn01 ብር 212,816.33 የመነሻ ሂሳብ በጥቅምት ወር 2011ዓ.ም በIBEX ለመጀመር በሚል በተሰብሳቢ ተመዝግቦ የሚታይ መሆኑ፣
- በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 0206372 በቀን 30/10/2011ዓ.ም በተቀጽላ ሌጀር ኮድ ብር SC03 ብር 33,408.16 ለስልጠና ተሳታፊዎች ከዋናው መ/ቤት የተላከ በሚል ተመዝግቦ የሚታይ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

<u>በሃዋሳ ቅ/ጽ/ቤት፣</u>

- በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 0847175 በቀን 30/08/2008 የምግብ ዋስትና ጥናት የሰራተኞች ደመወዝ ከግብርና ጥናት ፕሮጀክት የተከፈለ ብር 104,902.14፤ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 0847173 በቀን 08/07/2008 የምግብ ዋስትና ጥናት የስልጠና ውሎ አበል ከግብርና ጥናት ፕሮጀክት የተከፈለ ብር 263,235.24 ፤
- በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 16511 በቀን 30/10/2008 የሶሽዮ ኢኮኖሚ ጥናት የሰራተኞች ደመወዝ፤ የውሎ አበልና ትራንስፖርት ፤ የቀን ሙያተኞች እና የነዳጅ ወጪዎች ብር 894,260.40 እና በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 404969 በቀን 30/10/2009ዓ.ም ከግብርና እድገት ጥናት (ከኤ.ጂ.ፒ) ለስራ ማስኬያጃ በተሰብሳቢ ሂሳብ ከተያዘ ብር 127,524.17 ውስጥ 102,824.88 የተወራረደ ሲሆን ቀሪው 24,699.29 ያልተወራረደ መሆኑ፤

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 1,742,461.93 ከ2009 እስከ 2012 በጀት ዓመት ጀምሮ በመክፍቻ ሂሳብ (Opening Balance) እየዞረ የመጣና ተሰብሳቢ ሂሳብ ተብሎ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ (ጄቪ) የተመዘገበ ቢሆንም ተሰብሳቢ ሂሳብ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያለመቻሉ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

7. <u>የሂሳብ እንቅስቃሴ የሌላቸው ወይም የተቋረጡ ፕሮጀክት ላይ የሚታይ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

በሂሳብ መደብ 4274 በ22 የተለያዩ የፕሮጀክት ሂሳቦች ላይ በድምሩ ብር 15,742,164.29 ከአንድ ዓመት በላይ እንዲሁም በድምሩ ብር 3,467,534.45 ከአምስት ዓመት በላይ በአጠቃላይ በድምሩ ብር 19,209,698.74 የፕሮጀክቶቹ ሂሳብ ተጠናቆ ሳለ በተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

8. <u>የሂሳብ እንቅስቃሴ የሌላቸው ወይም የተቋረጡ ፕሮጀክት ላይ የሚታይ ተከፋይ ሂሳብ፤</u>

በሂሳብ መደብ 5002 በ22 የተለያዩ የፕሮጀክት ሂሳቦች ላይ በደምሩ ብር 17,588,221.07 ከአንድ ዓመት በላይ እንዲሁም በድምሩ ብር 3,059,805.48 ከአምስት ዓመት በላይ በአጠቃላይ በድምሩ ብር 20,648,026.55 የፕሮጀክቶቹ ሂሳብ ተጠናቆ ሳለ በተከፋይ ሂሳብ የሚታይ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

9. <u>ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል:: በተጨማሪም በፌዴራል መንግስት ግንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት አገልግሎት መ/ቤቱ በጀቱን የሚቆጣጠር መሆኑን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው ከ10% በላይ ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፦ በየፕሮግራሙ በተመለከቱት በተለያዩ የሂሳብ አርዕስቶች በበጀት ዓመቱ ለአገልግሎቱ ከተደለደለው መደበኛ በጀት ብር 1,874,308.74 ከካፒታል በጀት ብር 38,572,471.9 በድምሩ ብር 40,446,780.64 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ በኦዲት ታውቋል፡፡

<u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>

1. <u>የንብረት አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ፣</u>

በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 2 ንብረት አመዘጋገብና አሰተዳደር ፤አንቀጽ 3 የስቶክ አስተዳደር እንዲሁም አንቀጽ 5 የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም ፣ የመቆጣጠር እና አገልግሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንደሚገባ ይገልፃል፡፡ በዚሁ መሰረት የአገልግሎቱ የንብረት አያያዝ ፣ አጠቃቀም እና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ፦

በዋናው መ/ቤት

- የቋሚ፣ አላቂ እንዲሁም ለመረጃ መሰብሰቢያ የሚጠቀሙባቸው ታብሌቶች የተቀመጡበት 2 መጋዘኖች ንብረቶቹ በትክክል ለብልሽት በማይዳርግ ከመሬት ከፍታ ባለው ሽልፍ ያልተቀመጡ መሆኑ፣
- ካለፈው በጀት አመት ኦዲት ሪፖርት ላይ የተለያዩ ዓይነት የሚወገዱ ንብረቶች የነበሩ ሲሆን የተወሰኑት ቢወገዱም አሁንም ብዛት ያላቸውና የተለያዩ ዓይነት ያላቸው መወገድ ያለባቸው ንብረቶች ሳይወገዱ በመጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣

በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት

- ንብረት ወደ ቅ/ጽቤቱ ገቢ ሲደረግም ሆነ ወጪ ሲደረግ በአንድ የንብረት ክፍል ሰራተኛ ብቻ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑ፣
- ወደ ቅ/ጽ/ቤቱ ሲገቡ በንብረት ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ ወይም ሞዴል 19 እንዲሁም ወደ ዋና መ/ቤት ሲመለስ በንብረት ወጪ ማደረጊያ ወይም ሞዴል 22 የማይመዘገቡ እና በተቃራኒው ከዋናው መ/ቤት ወደ ቅ/ጽ/ቤቱ ሲገቡ በሞዴል 22 እና ወጪ ሲሆኑ በሞዴል 19 የሚመዘገቡ መሆኑ፣
- የቋሚ፣ አላቂ፣ ተመላሽ እንዲሁም የሚወገዱ ዕቃዎች በአንድ ንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ ፤
- የኮምፒውተር ስፒከር 2፣ ፋክስ ማሽን 2፣ የኤሌክትሪክ ካልኩሌተር 4፣ ላፕቶፕ ኮምፒውተር 2፣ ስቴፕለር መምቻ 9፣ የግድግዳ ሰአት 2፣ ሞኒተር 6፣ የደም ናሙና መውሰጃ 5፣ ፈርስት ኤድ ኪት 2፣ የመኪና ባትሪ 2፣ መክተፊያ 2፣ አሮጌ ከመነዳሪ 26፣ ፍላሽ 4፣ አሮጌ ፕሪንተር 2፣ የዴል ኮምፒውተር ዴስክ ቶፕ ስክሪን 10፣ ሀርድ ዲስክ 04፣ አሮጌ ቸርኬ 1፣ ጎማ ከነቸርኬው 1፣ ጎማ 19 እና ኒሳን ሳፋይ 1 በንብረት ክፍል ውስጥ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ተብለው የተቀመጡ መሆኑ ፤
- በ2013 በጀት አመት የኦዲት ግኝት መወገድ ያለባቸው ንብረቶች ዝርዝር ውስጥ አብዛኛዎቹ በሽያጭ እና በማቃጠል የተወገዱ ቢሆንም ገመድ ቀለበት የሌለው ብዛት 164፣ ኮፒ ማሽን 2፣ ጥይት 8፣ የሰርቨር ዕቃ 2፣ ኮምፒውተር ስክሪን መከላከያ 2፣ ፕሮተራክተር 11፣ ማስመሪያ 19፣ ዳፕሊተር 3፣ ካንዴላ 25 ፤ ሲ ዲ እና ሚሞሪ ካርድ 8 ጂቢ ብዛት 31 ያልተወገዱ መሆኑ፣

በሃዋሳ ቅ/ጽ/ቤት

- ንብረት ወደ ቅ/ጽቤቱ ገቢ ሲደረግም ሆነ ወጪ ሲደረግ በአንድ የንብረት ክፍል ሰራተኛ ብቻ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑ፤
- የተለያየ የንብረት ክፍል ቢኖርም ቋሚ፣ አላቂ፣ ተመላሽ እና የሚወገዱ ዕቃዎች ተለይተው የማይቀመጡ መሆኑ ፤
- የብረት ችካል 36 ፣ ዴል ኮምፒውተር 2፣ ቴክኖ ታብሌት 4፣ ትሪንብል ጂኖ 3B ብዛት 1፣ ካፒ ኮምፒውተር 4፣ ጂፒ ኤስ 76 ብዛት 1፣ የፕላስቲክ ማስታጠቢያ 1 እና ብሎዎር ብዛት 1 ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ እና የማይችሉ ሳይለዩ በንብረት ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በ2013 በጀት አመት የኦዲት ግኝት መወገድ ያለባቸው ንብረቶች ዝርዝር ወስጥ አብዛኛዎቹ በሽያጭ የተወገዱ ቢሆንም ኮምፓሶች፣ የናሙና ከረጢት፣ ሳይንቲፊክ ካልኩሌተር፣ ተለጣፊ ሶኬት፣ የብረት መዶሻ፣ ፍላሾች፣ የኮምፒውተር ማውዝ፣ ብሊንድ ኦፊስ ሻተሮች፣ ሸራ ቦርዶች፣ ቴክላስት ታብሌቶች፣ እና የመኪና ታኮ ያልተወገዱ መሆኑ፣

በደብረ ብርሃን ቅ/ጽ/ቤት

- ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች በአንድ የንብረት ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑን፣
- ጎማ ብዛት 4፣ ባለሁለት ፔድ ስታል የቢሮ ጠረጴዛ 2፣ ባለአንድ ፔድ ስታል የቢሮ ጠረጴዛ 3 እና የብረት ካዝና ብዛት 1 እንዲሁም በ2013 በጀት አመት የኦዲት ግኝት መወገድ ያለባቸው ንብረቶች ዝርዝር ወስጥ አብዛኛዎቹ በሽያጭ፣ በስጦታ እና በማቃጠል የተወገዱ ቢሆንም የችርቻሮ ሚዛን ሳጥን ብዛት 93፣ ክሊፕ ቦርድ 1፣ የኤሌክትሪክ ካልኩሌተር 5፣ የፍሬን ሲሊንደር 1፣ ኤችፒ ላፕቶፕ 1 እና አገልግሎት የማይሰጥ ወንበር ብዛት 4 ተጠግነው አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ አገልግሎት እዲሰጡ ካልሆነም የሚወገዱ መሆናቸው ሳይለይ በንብረት ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣

በጅማ ቅ/ጽ/ቤት

- ንብረት ወደ ቅ/ጽ/ቤቱ ገቢ ሲደረግም ሆነ ወጪ ሲደረግ በአንድ የንብረት ክፍል ሰራተኛ ብቻ ምዝገባ የሚከናወንና እንዲሁም የሚጠበቅ መሆኑ፡፡
- የቋሚ፣ አላቂ ፣ ተመላሽ እንዲሁም የሚወገዱ ዕቃዎች በአንድ ንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ፣

በሶዶ ቅ/ጽ/ቤት

የቋሚ ፣ አላቂ ፣ተመላሽ እንዲሁም የሚወገዱ ዕቃዎች በአንድ ንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ፣

በአርባ ምንጭ ቅ/ጽ/ቤት

ቋሚ ንብረት የሚሰሩና የማይሰሩ፣ ተመላሽ የተደረጉ፣ እንዲሁም የሚወገዱ ዕቃዎች ተለይተው መቀመጥ ሲገባቸዉ በአንድ ንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ፣

በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት፣

- የቋሚ፣ አላቂ፣ ተመላሽ እንዲሁም የሚወገዱ ንብረቶች በአንድ ንብረት ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፤
- ንብረት ገቢ እና ወጪ /ሞዴል 19 እና ሞዴል22/ በአንድ ሰው የሚሰራ መሆኑ፣

በሐረር ቅ/ጽ/ቤት፤

- የቋሚ እና ተመላሽ ንብረቶች በአንድ ንብረት ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ቢን ካርድ ቢኖርም ምዝገባ ማደረግ የተቋረጠ መሆኑ፣

በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት

- የቋሚ፣ አላቂ፣ ተመላሽ እንዲሁም የሚወገዱ ንብረቶች በአንድ ንብረት ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ ፤የንብረት ክፍል ጥበት መኖሩ ፤
- ብዛታቸው 120 አይነት የሚሆኑ የተቀመጡ ቋሚ ንብረቶች መወገድ ሲገባቸው ለረጅም ጊዜ በንብረት መጋዘን ውስጥ ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑ፤
- ንብረት ገቢ እና ወጪ /ሞዴል 19 እና ሞዴል 22 /በአንድ ሰው የሚሰራ መሆኑ፤

በጭሮ ቅ/ጽ/ቤት

- የቋሚ፣ አላቂ፣ ተመላሽ እንዲሁም የሚወገዱ ንብረቶች በአንድ ንብረት ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ ፤የንብረት ክፍል ጥበት መኖሩ፣
- የንብረት መጋዘን እና የንብረት ክፍል ሃላፊ ቢሮ በ 1 ክፍል ውስጥ መሆኑ፣
- ንብረት ገቢ እና ወጪ /ሞዴል 19 እና ሞዴል22/ በአንድ ሰው የሚሰራ መሆኑ፣
- ብዛታቸው የማይታወቅ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማንዋሎች ከዋናው መ/ቤት የመጡ ከነሃሴ 2012 ዓ.ም ጀምሮ ለረጅም ግዜ በቢሮ ኮሪደር ያለ አገልግሎት ተቀምጠው መቆየታቸው፤

ዋጋቸው የማይታወቅ አገልግሎት ሰጥተው እንዲወገዱ የተወሰነባቸው ቋሚ ንብረቶች ታኒታ የእናቶችና የህፃናት ሚዛን ብዛት 20፣ የችርቻሮ ሚዛን ባለ16 ኪ.ግ ብዛት 50 ያለ አገልግሎት ንብረት ክፍል የተቀምጡ መሆኑ፤

2. <u>የተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅ፣</u>

የፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2002 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የመንግስት መ/ቤት በግዥ፣በስጦታ በዝውውር ተረክቦ ለሚጠቀምበት ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተለየ የግል ማህደር በመክፈት በማሕደሩ ውስጥ ቢያንስ የሚከተሉት መረጃዎች መዝግቦ ይይዛል፡፡ ከ‹‹ሀ›› እስከ ‹‹ሰ›› ያለውን ስንመለከት የተሽከርካሪው ዓይነትና ሞዴል፣ የጭነቱ ልክ (በሰው፣በኩንታል፣ በኪውቢክ ሜትር ወይም በሊትር ተለይቶ)፣ የቻሲና የሞተር ቁጥሮች ፣ የሚጠቀመው የነዳጅ ዓይነት ፣ የተገዛበት ወይም የመ/ቤቱ ባለቤትነት ስር የዋለበት ቀን እና ዓ.ም ፤ የተሽከርካሪው ዋጋ እና፣ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ፤ እነዚህ የተጠቀሱት መረጃዎች በበቂ ምክንያት ተሟልተው ያልተገኙ እንደሆነ ባሉት መረጃዎች መሰረት ርክክብ ከተፈጸመ በኃላ ተጠቃሚው መ/ቤት ያልተገኙትን መረጃዎች ዝርዝርና ምክንያት በተሽከርካሪው የህይወት ታሪክ ውስጥ መዝግቦ ይይዛል ፣ ያልተሟሉትን መረጃዎችም ተከታትሎ እንዲሟሉ ይገልጻል፡፡ እንዲሁም

ገንዘብ ሚኒስቴር በቀን 25/1/2014 በደብዳቤ ቁጥር ግ/ኢ/1/53/86 በመንግስት ግዢ አፈፃፀምና ንብረት አወጋገድ ዙሪያ የሚስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮችን ለመፍታት ባወጣው ሰርኩላር ቁጥር 2 ላይ መ/ቤቶች በ2014 በጀት አመት ማለትም እስከ ሰኔ 2014 አ/ም ድረስ ብቻ አገልግሎት ሰጥተው እንዲወገዱ የተወሰነባቸው ተሽከርካሪዎች በገንዘብ ጣሪያ ሳይገደብ በራሳቸው ጨረታ በማወጣት እንዲያስወግዱ ሰርኩላር አስተላልፉል በዚህም መሰረት የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ ለማየት ኦዲት ሲደረግ፡-

<u>በዋናው መ/ቤት፣</u>

- የሠሌዳ ቁጥር ኢ.ት4-01387 እና የሠሌዳ ቁጥር ኢ.ት4-02508 ፎርድ ፒካፕ ደብል ጋቢና ብዛት 02 ተሽከርካሪዎች ፤የሠሌዳ ቁጥር ቁጥር 4- 011078 ላንድክሮዘር ብዛት 01ተሽከርካሪ ፤ የሠሌዳ ቁጥር 4-01496 ላንድ ክሮዘር ቱኤች ብዛት 01 ተሽከርካሪ በአጠቃላይ 4 ተሽከርካሪዎች በአርጅና ምክንያት ያለ

አገልግሎት ቆመው የተገኙ መሆኑና በ2013 በጀት አመት ኦዲት ሪፖርት ላይ እንዲወገዱ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ ፤

- የሠሌዳ ቁጥር 4-ኢት16168(ቶዮታ ቪ8) የተሽከርካሪ የግል ማህደር ውስጥ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ወርሃዊ የነዳጅ የዘይትና የጥገና ወጪ መጠቃለያ ቅጽ 03 ፤የመንግስት ተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያና የመዘዋወሪያ ፈቃድ መስጫ ቅፅ 06 የሌለ መሆኑ፣
- የሠሌዳ ቁጥር ኢት4-26574፣ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 4-26575 ተሽከርካሪዎች የግል ማህደር ውስጥ የመንግስት ተሽከርካሪዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች መረከቢያ ቅፅ 01፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅና የዘይትና ኪ.ሜ መመዝገቢያ ቅጽ 02 የሌለ መሆኑ፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ወርሃዊ የነዳጅ የዘይትና የጥገና ወጪ መጠቃለያ ቅጽ 03 ፎርሙ በተሽከርካሪው የግል ማህደር ላይ ቢኖርም አገልግሎት ላይ ያልዋለ መሆኑን፣ የመንግስት ተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያና የመዘዋወሪያ ፈቃድ መስጫ ቅፅ 06 የሌላቸው መሆኑ፤
- የሠሌዳ ቁጥር ኢት 4-11057 ቶዮታ ስቴሽንዎገን መኪና ፣ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 4-15100 ቶዮታ ሃርድቶፕ መኪና ፤ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 4-17207 ፎርዲ ፒክ አፕ መኪና፣ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 4-16167 ቶዮታ አዉቶሞቢል መኪና፣ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 4-01243 ሚትስቡሽ ስቴሽንዎገን መኪና፣ የሠሌዳ ቁጥር 4-17528፤ የሠሌዳ ቁጥር4-03192 ፤የሠሌዳ ቁጥር4-18684 ፤የሠሌዳ ቁጥር 4-25189፣ የሠሌዳ ቁጥር 4-0891 የመንግስት ተሽከርካሪዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች መረከቢያ ቅፅ 01፤ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፤ የዘይትና የኪ.ሜ መመዝገቢያ ቅፅ 02 ፤የመንግስት ተሽከርካሪዎች ወርሃዊ የነዳጅ፤ የዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ ቅፅ 03፣ የመንግስት ተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያና የመዘዋወሪያ ፈቃድ መስጫ ቅፅ 06 የሌላቸው መሆኑ፣

__በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት__

- ተሽከርካሪዎች የግል ማህደር የሌላቸው መሆኑ፣
- የመንግስት ተሽከርካሪዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች መረከቢያ (ቅፅ 01)፤ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፤ የዘይትና የኪ.ሜ መመዝገቢያ (ቅፅ 02)፤ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ወርኃዊ የነዳጅ፤ የዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ (ቅፅ 03)፤ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ሕይወት ታሪክ መመዝገቢያ (ቅፅ 04)፤

የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ለተጠቃሚዎች መመደቢያ (ቅፅ 05)፣ የመንግስት ተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያና የመዘዋወሪያ ፈቃድ መስጫ (ቅፅ 06)፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የነዳጅ፣ የዘይትና ቅባት መጠየቂያ (ቅፅ 08)፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የጥገና መጠየቂያ (ቅፅ 09)፤የመንግስት ተሽከርካሪዎች የጥገና የሥራ ትዕዛዝ (ቅፅ 10)፣ የመንግስት ተሽከርካሪ የመለዋወጫ ዕቃ መጠየቅያ (ቅፅ 11)፣ በጥገና ወቅት የተለወጡ ዕቃዎች ሪፓርት ማቅረቢያ (ቅፅ 12) በትክክል የማይሞሉ ወይም የማይመዘገቡና በየተሽከርካሪዎቹ ማህደር የማይቀመጥ መሆኑ፣

- ተሽከርካሪዎቹ በዝውውር ከዋና መ/ቤት ወደ ቅ/ጽ/ቤቱ ሲገቡ በንብረት ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ ወይም ሞዴል 19 እንዲሁም አገልግሎቱን ጨርሶ ወደ ዋና መ/ቤት ሲመለስ በንብረት ወጪ ማደረጊያ ወይም ሞዴል 22 የማይመዘገቡ እና በተቃራኒው ከዋናው መ/ቤት ወደ ቅ/ጽ/ቤቱ ሲገቡ በሞዴል 22 እና ወጪ ሲሆኑ በሞዴል 19 የሚመዘገቡ መሆኑ፤

<u>በሃዋሳ ቅ/ጽ/ቤት፣</u>

- ተሽከርካሪዎቹ የግል ማህደር ቢኖራቸውም የተሽከርካሪው ርክክብ ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እስኪወገድ ድረስ በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን የነዳጅ፣ ዘይት እና ቅባት ፍጆታ መጠን፣ የጥገና ወጪ፣ የተጓዘው የኪ.ሜ መጠን፣ በአነማን ይዞታ ስር እንደነበረ ያልተሞላ መሆኑ፣
- የመንግስት ተሽከርካሪዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች መረከቢያ (ቅፅ 01)፤የመንግስት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፤ የዘይትና የኪ.ሜ መመዝገቢያ (ቅፅ 02)፤የመንግስት ተሽከርካሪዎች ወርኃዊ የነዳጅ፣ የዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ (ቅፅ 03)፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ለተጠቃሚዎች መመደቢያ (ቅፅ 05)፤የመንግስት ተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያና የመዘዋወሪያ ፈቃድ መስጫ (ቅፅ 06)፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የነዳጅ፣ የዘይትና ቅባት መጠየቂያ (ቅፅ 08)፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የጥገና መጠየቂያ (ቅፅ 09)፤የመንግስት ተሽከርካሪዎች የጥገና የሥራ ትዕዛዝ (ቅፅ 10)፣ የመንግስት ተሽከርካሪ የመለዋወጫ ዕቃ መጠየቅያ (ቅፅ 11)፣ በጥገና ወቅት የተለወጡ ዕቃዎች ሪፓርት ማቅረቢያ (ቅፅ 12) በተወሰኑ የተሽከርካሪ ማህደር ላይ የተወሰኑ ቅጾች የተሞሉ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት ሙሉ በሙሉ ያልተሞሉ መሆኑ፣

በደብርሃን ቅ/ጽ/ቤት

- ተሽከርካሪዎች የግል ማህደር የሌላቸው መሆኑ፣
- የመንግስት ተሽከርካሪዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች መረከቢያ (ቅፅ 01)፤የመንግስት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፤ የዘይትና የኪ.ሜ መመዝገቢያ (ቅፅ 02)፤የመንግስት ተሽከርካሪዎች ወርኃዊ የነዳጅ፣ የዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ (ቅፅ 03)፤የመንግስት ተሽከርካሪዎች ሕይወት ታሪክ መመዝገቢያ (ቅፅ 04)፤የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ለተጠቃሚዎች መመደቢያ (ቅፅ 05)፤የመንግስት ተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያና የመዘዋወሪያ ፈቃድ መስጫ (ቅፅ 06)፤የመንግስት ተሽከርካሪዎች የነዳጅ፤ የዘይትና ቅባት መጠየቂያ (ቅፅ 08)፤ የመንግስት ተሽከርካሪዎች የጥገና መጠየቂያ (ቅፅ 09)፤የመንግስት ተሽከርካሪዎች የጥገና የሥራ ትዕዛዝ (ቅፅ 10)፤የመንግስት ተሽከርካሪ የመለዋወጫ ዕቃ መጠየቂያ (ቅፅ 11)፤በጥገና ወቅት የተለወጡ ዕቃዎች ሪፓርት ማቅረቢያ (ቅፅ 12) በትክክል ተሞልተው በየተሽከርካሪዎቹ ማህደር ያልተቀመጡ መሆኑ፤

በጅማ ቅ/ጽ/ቤት

- የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-02619 ፎርድ መኪና ከሁለት ዓመት በላይ ያለአገልግሎት የቆመ መሆኑ፤
- የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-02507 ፎርድ የሚሰራ ተሽከርካሪ ከ1 ወር በላይ ያለ አገልግሎት የቆመ መሆኑ፣

በአርባ ምንጭ ቅ/ጽ/ቤት

- የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-01222 ሬንጀር ተሽከርካሪ ለ1 ዓመት ያህል ያለአገልግሎት የቆመ መሆኑ፤

በሶዶ ቅ/ጽ/ቤት፣

- የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-01236 ፎርድ ረንጀር መኪና ከአራት ወር በላይ ያለ አገልግሎት የቆመ መሆኑ፣
- የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-01486 ኒሳን ፓትሮል መኪና ከአምስት ወር በላይ ያለአገልግሎት የቆመ መሆኑ፤

__በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት፣__

- የሰሌዳ ቁጥር 4-01946፣ 4-15089፣ 4-18323፣እና 4-11074 በማህደራቸው ውስጥ የህይወት ታሪክ መዝገብ ቅጽ 04 ያልመዘገበ መሆኑ ፤
- የሰሌዳ ቁጥር 4-01946፣ 4-15089 እና 4-11074 በማህደራቸው የዕቃ ገቢ ማድረጊያ ደረሠኝ (ሞዴል 19) አለመኖሩ ወይም በኮፒ አለመያዙ፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-01946 ፣ 4-15089፣ 4-18323 እና 4-11074 በማህደራቸው ውስጥ የህይወት ታሪክ መዝገብ ቅጽ 04 ላይ የህይወት ታሪክ መዝገብ ማለትም ቅጽ 04 ባለመኖሩ የተመዘገበ ቅጹ ላይ የሚመዘገቡ የመ/ቤቱ ባለቤትነት ሥር የዋለበት ቀን እና ዓ/ም፣ የተሽከርካሪው ዋጋ፣ እንዲሁም በኪሎ ሜትር የሚጠቀመውን ነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት ፍጆታ መጠን፣ የጥገና ወጪ፣ የተጓዘው ኪ.ሜ መጠን፣ በእነማን ይዞታ ስር እንደነበረ እና ከቅጽ 3 ጋር የማይነጻጸር መሆኑ በኦዲት ማወቅ ተችሏል፡፡
- የሰሌዳ ቁጥር ኢት-4/01946 ከግንቦት /2013 ጀምሮ በብልሽት የቆመ ሲሆን በ19/1/2014 በደብዳቤ ቁጥር 1.8.28/434 ተሽከርካሪው መወገድ እንዳለበት ተወስኖበት ለረጅም ግዜ ያለአገልግሎት ቆሞ መቆየቱ፤

__በሐረር ቅ/ጽ/ቤት፣__

- የሰሌዳ ቁጥር 4-15088፣ 4-09016፣ 4-11063፣እና 4-11152 በማህደራቸው ውስጥ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፣ የዘይትና የኪ.ሜ መመዝገቢያ ቅጽ 02፣ የመንግስት ተሽከርካሪ ወርኃዊ የነዳጅ ፤ ዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ ቅጽ 03 በማህደር ውስጥ የለለ መሆኑ፣ እንዲሁም የህይወት ታሪክ መዝገብ ቅጽ 04 ያለ ቢሆንም የህይወት ታሪክ መዝገብ ላይ ባልተሟላ መልኩ ማለትም በቅጹ ላይ ሊሟሉ ከሚገቡት ውስጥ የተገዛበት ቀን፣ የተገዛበት ዓ.ም፣ እና በቀጹ ላይ የለው ሠንጠረዥ በሠንጠረዡ ላይ የሚሞሉ ከቅጽ 03 ጋር የማይነጻጸር መሆኑን እና በማህደራቸው ውስጥ የዕቃ ገቢ ማድረጊያ ደረሠኝ (ሞዴል 19) አለመኖሩ ወይም በኮፒ አለመያዙ፣
- የሰሌዳ ቁጥር ኢት-4-01421 ኒሳን ሰፋሪ ለረዥም ዓመት ያለአገልግሎት መቆሙን በቀን 08/08/2013 በደብዳቤ ቁጥር ሐማብሎ-4/5162013 ለዋና መ/ቤት እንዲወገድ ያሳወቁ ቢሆንም ምንም ዓይነት እርምጃ አለመወሰዱን እና አለመወገዱን በኦዲት ወቅት ማወቅ ተችሏል እንዲሁም የሰሌዳ ቁጥር ኢት-

09016 ፎርድ ሬንጀር ተሽከርካሪ ከግንቦት 2013 ዓ.ም ጀምሮ በብልሽት የቆመ መሆኑን በ25/1/2015 በደብዳቤ ቁጥር ሐ/ለ-4/108/2015 ለዋና መ/ቤት ያሳወቁ ቢሆንም ምንም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

__በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት፣__

- በሠሌዳ ቁጥር 4-11099፣ 4-03801፣ 4-15898 እና 4-22165 የግል ማህደር ውስጥ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነጃጅ ፣ የዘይትና ኪ.ሜ መመዝገቢያ ቅጽ 02 ፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ወርሃዊ የነዳጅ የዘይትና የጥገና ወጪ መጠቃለያ ቅጽ 03 የሌለ መሆኑ፣ የመንግስት ተሽርካሪዎች ህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ቅጽ 04 ያለ ቢሆንም መሟላት ካለበት ውስጥ የተገዛበት ዋጋ እና የተገዛበት ቀንና ዓ.ም ያልተመዘገበ መሆኑ፣ ተሽከርካሪው ገቢ የሆነበት የዕቃ ገቢ ማድረጊያ ሞዴል 19 ከማህደሩ ውስጥ ያልተያያዘ መሆኑ፡፡
- በሠሌዳ ቁጥር 4-32830፣ የግል መህደር ውስጥ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነጃጅ፣ የዘይትና ኪ.ሜ መመዝገቢያ ቅጽ 02፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ወርሃዊ የነዳጅ የዘይትና የጥገና ወጪ መጠቃለያ ቅጽ 03፣ የመንግስት ተሽርካሪዎች ህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ቅጽ 04 የሌለ መሆኑ፣
- በሠሌዳ ቁጥር 4-32831፣ የግል መህደር ውስጥ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ወርሃዊ የነዳጅ የዘይትና የጥገና ወጪ መጠቃለያ ቅጽ 03 እና የመንግስት ተሽርካሪዎች ህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ቅጽ 04 የሌለ መሆኑ፣

__በጭሮ ቅ/ጽ/ቤት__

- የሰሌዳ ቁጥር 4-24831፣4-32836 በማህደራቸው ውስጥ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፣ የዘይትና የኪ.ሜ መመዝገቢያ ቅጽ 02፣ የመንግስት ተሽከርካሪ ወርኃዊ የነዳጅ፣ የዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ ቅጽ 3፣ በማህደር ውስጥ የለለ መሆኑ፣ እንዲሁም የህይወት ታሪክ መዝገብ ቅጽ 04 እና የዕቃ ገቢ ማድረጊያ ሞዴል 19 በማህደር ውስጥ የሌለ መሆኑ፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-02424፣ 4-11153፣ እና 4-02628 በማህደራቸው ውስጥ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፣ የዘይትና የኪ.ሜ መመዝገቢያ ቅጽ 02፣ የመንግስት ተሽከርካሪ ወርኃዊ የነዳጅ፣ ዘይትና የጥገና ወጪ ማጠቃለያ ቅጽ 3 በማህደር ውስጥ የሌለ መሆኑ፣ እንዲሁም የህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ቅጽ 04 ያለ ቢሆንም የህይወት ታሪክ መዝገብ ላይ ባልተሟላ መልኩ ማለትም

በቅጹ ላይ ሊሟሉ ከሚገቡት ውስጥ፣ እና በቅጹ ላይ ያለው በሠንጠረዡ ላይ የሚሞሉ ከቅጽ 03 ጋር የማይነጻጸር መሆኑን እና በማህደራቸው ውስጥ የዕቃ ገቢ ማድረጊያ ደረሠኝ (ሞዴል 19) አለመኖሩ ወይም በኮፒ አለመያዙ ፤

- የሰሌዳ ቁጥር ኢት-4-09047 ፎርድ ፒክአፕ ከሶስት ዓመት በላይ ያለ አገልግሎት መቆሙን በቀን 07/01/2011 በደብዳቤ ቁጥር ዐ.ተሰታ.11/174/2011 ለዋና መ/ቤት ተሽከርካሪው መቆሙን ያሳወቀ ቢሆንም ምንም ዓይነት እርምጃ አለመወሰዱን እና አለመወገዱ፣

በኦዲት ታውቋል፡፡

3. <u>በመመሪያው ከተፈቀደው መጠን በላይ ወጪ የተደረገ የኃላፊዎች ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ፣</u>

በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት በቀን 19/03/2012 ዓ.ም በቁጥር መ30-899/11 በተጻፈው ደብዳቤ የኢፌድሪ ሚኒስቴሮች ምክር ቤት ነሐሴ 1/2011ዓ.ም የከፍተኛ መንግስት ኃላፊዎች የደመወዝና ጥቅማጥቅም ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያው አስመልክቶ የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶችን ከሚመሩ ኃላፊዎች ጥቅማጥቅም ጋር በተያያዘ በተለይም የቤተሰብ ተሽከርካሪ እንደማይመደብላቸው እየታወቀ አዲስ በተሻሻለው መመሪያ አንቀጽ 7 ንሁስ አንቀጽ 2 እንደማያካትታቸው ተቆጥሮ የሚመለከታቸው አንዳንድ መ/ቤቶች ጥያቄ እያቀረቡ መሆኑን በመጥቀስ የተሻሻለው ጥቅማ ጥቅም መመሪያ የ1997 ዓ.ም እና የ2004 ዓ.ም መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ስለሆነ ለዋና ዳይሬክተሮች እና ለም/ዋና ዳይሬክተሮች የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ አንድ ተሽከርካሪ ከሚመደብ በስተቀር ለቤተሰቦቻቸው የሚመደብ ተሽከርካሪ እንደሌለ ይገልፃል፡፡

ይሁን እንጂ መ/ቤቱ በአንድ ዋና ዳይሬክተርና በሶስት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች በሹፌሮቻቸው ስም በእያንዳንዳቸው አንዳንድ ተሽከርካሪ መስጠት ሲገባው ሁለት ሁለት ተሽከርካሪ የያዙ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

4. <u>የአገልግሎቱ ነባር እና አዳዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ፣</u>

ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሐምሌ/2009 በ2010 በጀት ዓመት ላይ ወጪን ለመቀነስ የተዘጋጀ የአዘገጃጀትና የአቀራረብ መመሪያ የካፒታል ወጪን በተመለከተ

አንቀጽ 4/ ተራ ቁጥር 1 ፕሮጀክቶች በታቀደው ጊዜ፣ ወጪ እና ጥራት እንዲከናወኑ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ስርዓትን በማጠናከር አስፈጻሚ አገልግሎቱ ከስራው ተቋራጩ እና አማካሪው ድርጅት ጋር በጋራ የስራ አፈጻጸሙን በየጊዜው በመገምገም ፕሮጀክቱ ተጨማሪ ወጪ እና ጊዜ እንዳያስከትል መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003ዓ.ም አንቀጽ 7/2 ፊደል ሀ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ያከናወኑዋቸውን የግንባታ ስራዎች እንደ ቋሚ ንብረቶች በተለየ መዝገብ መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ፡-

<u>በዋናው መ/ቤት</u>

- በነባር የግንባታ ፕሮጀክቶች ማለትም በፌዴራል መንግስት ህንጻዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት እና በSFR ፕሮጀክት የተገነቡ ህንጻዎች ጊዜያዊ እና የመጨረሻ ርክክብ የተደረገባቸው ሙሉ ህጋዊ ማስረጃዎች ፤
- ህንጻዎቹ የአገልግሎቱ ለመሆናቸው በሚረጋገጥበት ሁኔታ በንብረት ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ /ሞ-19/ በተጨማሪም በቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድ / Fixed Asset Registration Card-FAR/ እና የተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ/Fixed Asset with user Control Card -UC/ ለመመዝገባቸው ማስረጃዎቹ ያልቀረቡ መሆኑ ፤

<u>በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- የቢሮ ህንጻ ግንባታ ተጠናቆ ነሐሴ /2012 ዓ.ም አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ ቢገለጽም ህንጻው ጊዜያዊና የመጨረሻ ርክክብ ከህንፃ ተቋራጩ ጋር ያልተደረገ መሆኑ፣
- በህንፃው የመጨረሻ ወለል(5ኛ ፎቅ) ላይ በግራና በቀኝ ያሉት በረንዳዎች የወለሉ ተዳፋት(Slop) በትክክል ባለመሰራቱ በረንዳው ውሃ እያቆረ ወደ 4ኛ እና 3ኛ ወለል ፍሳሽ በመግባት ህንፃው እየተበላሸ መሆኑ፣
- በህንጻው ላይ የተሰሩት የመጸዳጃ ቤቶች አየር ማስተንፈሻ ያልተሰራላቸው መሆኑና ዲናሞ ባለመስራቱ ውሃ ወደ ላይ እና ወደታች ባለመውጣቱ መጸዳጃ ቤቶቹ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፣
- በህንፃው ላይ የተገጠመው አዲስ አሳንሰር (ሊፍት) አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣
- በምድር ቤት አካባቢ የተሰሩ ሶስት የመጸዳጃ ቤቶች ውሃ ወደ ላይ የሚተፉ እና የአሰራር ችግር ያለባቸው በመሆኑ ተገቢውን አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ

በሃዋሳ ቅ/ጽ/ቤት

- የቢሮ ህንጻ ግንባታ ተጠናቆ ነሐሴ 20/2009 ዓ.ም ተመርቆ አገልግሎት እየሰጠ ቢሆንም ህንጻው ጊዜያዊና የመጨረሻ ርክክብ ያልተደረገለት መሆኑ፣
- በህንፃው የመጨረሻ ወለል(4ኛ ፎቅ) ላይ በግራና በቀኝ ያሉት በረንዳዎች ጣሪያ(Shed) ያልተሰራለት በመሆኑ ፍሳሽ ወደ 3ኛ ወለል ላይ በመግባት የህንፃው ግድግዳ በከፍተኛ ሁኔታ እያበላሸው መሆኑና ፍሳሹ ወደ 2ኛ ወለል ላይም እየወረደ መሆኑ እንዲሁም በህንፃው በጀርባ በኩል ከላይ እስከታች በዚህ በሚመጣው ፍሳሽ ግድግዳው እየበሰበሰና እየፈረሰ መሆኑ፤ በአጠቃላይ የቅ/ጽ/ቤቱ ህንፃ ትኩረት ተሰጥቶት በአስቸኳይ ካልተሰራ የመፍረስ አደጋና ከጥቅም ውጭ ሊሆን እንደሚችል ታውቋል።

5. የክትትል ኦዲት በተመለከተ፤

በ2013 በጀት ዓመት ለህዝብና ቤት ቆጠራ አገልግሎት እንዲውል ለተገዛው ታብሌት እንዲጠብቁ እና እንዲቆጣጠሩ ለተመደቡት የፌደራል ፖሊስ አባላት የሰርቪስ አገልግሎት እንዲሰጡ ለተመደቡ የኤጀንሲው ሹፌሮች የውሎ አበል ክፍያ በድምሩ ብር 59,292.00 የቁርስ፣ የምሳ፣ የእራት የተከፈለው ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

የህግ ጉዳዮች በተመለከተ(Compliance Issue)፣

1. ተጨማሪ ውል ሳይያዝ የተፈጸመ የተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት ግዥ ክፍያ በተመለከተ

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻፀም መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀፅ 25.2 ፊደል ሀ እስከ መ መሰረት ፡ በአይነት እና በዋጋ አንድ የሆኑ ዕቃዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ የግንባታ ዘርፍ ስራዎችን እና የምክር አገልግሎቶችን ቀደም ሲል እነዚህን ካቀረበው ተጫራች መግዛት ጠቃሚ መሆኑ ሲታመንበት በአቅራቢው ፈቃደኝነት ላይ በመመስረትና ከሀ-መ በተዘረዘሩት መሰረት አገልግሎቱ እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ የግዥ ወጪዎች በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡- በዋናው መ/ቤት በድምሩ ብር 4,844,353.15 የተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት ግዥ ቀድሞ በጨረታ ካሸነፉት ድርጅቶች ከጁፒተር እና ከአዲያማት ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በተጨማሪ ለታዘዘው አገልግሎት ግዥ ተጨማሪ ውል

ሳይያዝ ከውሃና መስኖ ኢነርጂ ሚኒስቴር ከተገኘው (MoW) የፕሮጀክት ሂሳብ ግዥ በማከናውን ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

2. የውስን ጨረታ መስፈርት ያላሟላ ግዥ በተመለከተ፣

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግሥት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 23 የውስን ጨረታ ግዥ አፈጻጸም መመሪያ በንዑስ አንቀጽ 23.2.1 ፊደል ለ መሠረት በጨረታው ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር በርካታ ቢሆኑም ግዥው በንዑስ አንቀጽ 23.3 በተቀመጠው የገንዘብ መጠን ገደብ ውስጥ ከሆነ አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡት መካከል ፍትሐዊ በሆነ ምርጫ ቢያንስ አምስት ዕጩ ተወዳዳሪዎች መመረጥ እንደሚኖርበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በአገልግሎት መ/ቤቱ የጭሮ ቅርጫፍ ጽ/ቤት በቀን 30/9/2014 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 154224 በብር 91,190.00 /ዘጠና አንድ ሺ አንድ መቶ ዘጠና / የደንብ ልብስ ሲገዛ የውስን ጨረታ ውድድሩ በመመሪያው ከተጠቀሰው ባነሰ ሶስት (3) አቅራቢዎች (ተወዳዳሪዎች) ብቻ በማወዳደር ግዥ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

3. ዝቅተኛ ተብሎ የተመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ሳይረጋገጥ በዋጋ ማወዳደሪያ የግዥ ዘዴ የተፈጸመ ግዥ በተመለከተ፣

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻፀም መመሪያ ክፍል 5 አንቀጽ 24(8) መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈፅማቸው ግዥዎች ኤጀንሲው በድህረ-ገፅ የሚያወጣውን ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር፤ በግዥ ስራ ክፍሉ የሚካሄድ የገበያ ጥናት በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማመን እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መመሪያ አንቀፅ 8 ንኡስ አንቀፅ 24(3) ላይ እንደተቀመጠው የመንግስት መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ ሲፈጽም በውድድሩ ተሳታፊ የሚሆኑት አቅራቢዎች ከአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የሚመረጡ ሆኖ እስከተቻለ ድረስ ቁጥራቸው ከሶስት ማነስ እንደሌለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በአገልግሎት መ/ቤቱ፡-

1. በዋናው መ/ቤት(ከፕሮጀክት ሂሳብ)
    - ከሶስተኛ ወገን ከመጡ የእርዳታ የፕሮጀክት ሂሳቦች ለእቃና የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ብር 1,479,100.96

2. **በቅርጫፍ ጽ/ቤቶች (ከመደበኛ በጀት)፤**

- በአዳማ በቅርጫፍ ጽ/ቤት በድምሩ ብር 133,269.04፣
- በሃዋሳ በቅርጫፍ ጽ/ቤት በድምሩ ብር 199,820.24፣
- በደ/ብርሃን በቅርጫፍ ጽ/ቤት በድምሩ ብር 201,011.37፣
- በጅማ በቅርጫፍ ጽ/ቤት በድምሩ ብር 494,346.79፣
- በወላይታ ሶዶ በቅርጫፍ ጽ/ቤት በድምሩ ብር 922,690.58፣
- በአርባ ምንጭ በቅርጫፍ ጽ/ቤት ብር 302,514.06፣
- በጭሮ በቅርጫፍ ጽ/ቤት ብር 148,210.56፣
- በድሬዳዋ በቅርጫፍ ጽ/ቤት በድምሩ ብር 60,212.43፣
- በሐረር በቅርጫፍ ጽ/ቤት በድምሩ ብር 58,448.50 እና
- በጅግጅጋ በቅርጫፍ ጽ/ቤት በድምሩ ብር 93,603.74፣

➡ በአጠቃላይ በድምሩ ብር 2,465,916.75 የተለያዩ የእቃ እና የአገልግሎት ግዥዎች በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ሲፈፅም በግዥ ስራ ክፍሉ የገበያ ጥናት እና በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ከሚወጣው ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር ወይም የገበያ ጥናት በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑ ሳይረጋገጥ እንዲሁም በግዥ ክፍሉ በሚዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ማወዳደሪያ ሰንጠረዥ እና ቃለ-ጉባኤ ላይ የፋይናንሽያል ግምገማ እንጂ አቅራቢዎች ያቀረቧቸው የሕጋዊነት ብቃት ማስረጃዎች ወይም ሰነዶች ትክክል ለመሆናቸው ቅድመ ግምገማው (Primary evaluation) ሳይደረግ በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፣

➡ በጭሮ ቅ/ጽ/ቤት በቀን 03/04/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 64801 ብር 45,736.96 ለስልጠና ተሳታፊዎች ሪፍሬሽመንት የሚሆን የሆቴል አገልግሎት ግዥ ሲከናወን ሁለት ድርጅቶች ብቻ የተወዳደሩ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

4 **በጨረታ መገዛት ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ**

የገንዘብ ሚንስቴር በቀን 25/01/2014 ባወጣው የግዥ ማሻሻያ መመሪያ በዋጋ ማቅረቢያ የሚገዛው ምክር ያልሆነ የአገልግሎት ግዥ የገንዘብ ጣሪያ (Treshold) ብር 300,000.00 /ሶስት መቶ ሺህ/ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ አገልግሎቱ በመመሪያው መሰረት ግዥዎችን የሚፈጽም መሆኑ ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

- በአዳማ በድምሩ ብር 1,825,337.29 የሆቴል መስተንግዶ/አገልግሎት ግዥ፤

- በወላይታ ሶዶ በቀን 12/01/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 489699 ብር 409,592.83 የሆቴል መስተንግዶ አገልግሎት ግዥ፤
- በአርባ ምንጭ በቀን 12/09/2014 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 523671 ብር 442,262.40 የሆቴል መስተንግዶ አገልግሎት ግዥ፤
- በድሬድዋ በቀን 20/05/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 692579 በድምሩ ብር 505,577.71 የሆቴል መስተንግዶ አገልግሎት ግዥ፤
- በሐረር በቀን 10/01/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 87936 በድምሩ ብር 334,880.00 የሆቴል መስተንግዶ አገልግሎት ግዥ፤

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 3,517,650.23 ለተለያዩ ጥናቶች ለተቆጣጣሪና ለመረጃ ሰብሳቢዎች በተሰጠው ስልጠና ለሆቴል መስተንግዶ ግዥ በጨረታ መፈጸም ሲገባው ከመመሪያ ውጪ በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

5 <u>ያለውድድር በቀጥታ የተፈጸመ የተሽከርካሪዎች ጥገና ግዥን በተመለከተ፣</u>

ገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ጠበ47/41/6/24 በቀን 10/08/2011 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ መሰረት የፌዴራል መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ህግና መመሪያውን በመጠበቅ እንዲሁም ገንዝብ ሊያስገኝ የሚችለውን ዋጋ ግምት ውስጥ በማስገባት ከተፈቀዱ የግዥ ዘዴዎች ውስጥ ተስማሚ የሆነ የግዥ ዘዴ በመጠቀም የተሽከርካሪዎችን ጥገና ማድረግ እንሚቻል ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ በአገልግሎት መ/ቤቱ፡-

- በሃዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በቀን 28/10/2014ዓ.ም በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 533908 በሂሳብ መደብ 6241 ብር 135,000.00 የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ጥገና ለአሸናፊ ገልገሎ ሁለገብ ጋራዥ በቀጥታ ያለ ውድድር የጥገናው ሥራ የተሰጠና ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት በቀን 16/4/2014 በባንክ ወጪ ማመሳከሪያ ቁጥር 01875 በሂሳብ መደብ 6241 ከአንዋር አጠቃላይ የመኪና መለዋወጫ ብር 19,895.00 የተሽከርካሪ መለዋወጫ ግዥ እና በቀን 11/6/2004 በባንክ ወጪ ማመሳከሪያ ቁጥር 01962 በሂሳብ መደብ 6241 ከአማረ ተደነቀ ጋራጅ ብር 22,800.00

የተሽከርካሪ ጥገና የአገልግሎት ግዥ በድምሩ ብር 42,695.00 በቀጥታ ያለ ውድድር ጥገናው የተፈጸመ መሆኑ፣

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 177,695.00 በቀጥታ ያለ ውድድር የጥገናው ሥራ የተሰጠና ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

6. ከተለያዩ ግዥዎች ክፍያ ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ፤

በገዢዉ ተይዞ ስለሚከፋል ተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 60/2012 አንቀጽ 5 ተራ ቁጥር 1 ማንኛዉም ወኪል ለአቅራቢዉ መክፈል ካለበት የተጨማሪ እሴት ታክስ ዉስጥ 50% (ሀምሳ በመቶ) ብቻ ቀንሶ በማስቀረት ያስቀረውን ታክስ በየወሩ የሚቀጥለዉ ወር በገባ በ30 ቀናት ውስጥ በታክስ ከፋይነት ለተመዘገበበት የታክስ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለበት በማለት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ፡-

በአርባ ምንጭ ቅ/ጽ/ቤት፤

- በቀን 30/03/2014 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 447231 ብር 26,599.50 ከ ሳሮ ሕንፃ መሳሪያ (ተህዩ ሙጀባ) ሜትር የተገዛና ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን አቅራቢዉ ባቀረበዉ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 3,469.5 መቆረጡን ቢያሳይም ቅ/ጽ/ቤቱ 50% (ሀምሳ በመቶ) ብር 1,734.75 ቀንሶ በማስቀረት በሂሳብ መደብ 5059 መዝግቦ ያልያዘ እና ለሚመለከተዉ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ያላደረገ መሆኑ፣
- በቀን 30/10/2014 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 731192 ብር 23,000.00 ከስንታየሁ ዳዲዎ የፅዳት እቃዎች ጅምላ ንግድ ሳሙና የተገዛና ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን አቅራቢዉ ድርጅት ባቀረበዉ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 3,000.00 መቆረጡን ቢያሳይም ቅ/ጽ/ቤቱ 50% (ሀምሳ በመቶ) ብር 1,500.00 ቀንሶ በማስቀረት በሂሳብ መደብ 5059 መዝግቦ ያልያዘ እና ለሚመለከተዉ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ያላደረገ መሆኑ፣
- በቀን 30/10/2014 በሒሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 731358 ብር 33,082.4 ከ ቬኑስ ብትን ጨርቃጨርቅ እና ልብስ ስፌት የደንብ ልብስ ግዥ የተገዛና ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን አቅራቢዉ ድርጅት ባቀረበዉ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 4,315.1 መቆረጡን ቢያሳይም ቅ/ጽ/ቤቱ

50% (ሀምሳ በመቶ) ብር 2,157.55 ቀንሶ በማስቀረት በሂሳብ መደብ 5059 መዝግቦ ያልያዘ እና ለሚመለከተዉ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ያላደረገ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 5,392.30 የተጨማሪ እሴት ታክስ ከክፍያው ላይ ያልተቀነሰ እና ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

7. <u>በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/4 ፊደል መ የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት የመደበኛ እና የፕሮጀክት ሂሳብ የተሰብሳቢ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ፡-

1. <u>ከመደበኛ ሂሳብ፣</u>
   በዋናው መ/ቤቱ የተጠቃለለው ሂሳብ ሪፖርት ላይ፡-

- በሂሳብ መደብ 4201(5217301) ብር 3,053.62 ከ10 አመት በላይ፣
- በሂሳብ መደብ 4210 (5217109)ብር 657,739.97 ከ10 አመት በላይ፣
- በሂሳብ መደብ 4211(5217110)ብር 2,645,636.57 ከአንድ ዓመት በላይ ፤
- በሂሳበ መደብ 4253(5217205) ብር 196,815.68 ከአንድ አመት በላይ ፤
- በሂሳብ መደብ 4274(5217399) ብር 22,333,881.10 ከአንድ ዓመት በላይ

በድምሩ ብር 25,837,126.94 በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣

2. <u>ከፕሮጀክት ሂሳብ፣</u>

- በሂሳብ መደብ 4210 ከFinger print ብር 1,113,962.38 ፤ ከSocio ፕሮጀክት ብር 29,991.79 ፤ ከFS12 ብር 5,767,670.62 ፤ ከCALM ብር 127,826.28 እና ከIPF 1,390,631.89 በድምሩ ብር 8,430,082.96 ከአንድ ዓመት በላይ ፤
- በሂሳብ መደብ 4211 ከFinger print ብር 38,994.77 ፤ ከSocio ብር 37,159.36 ፤ከ FS12 ብር 258,756.02 በድምሩ ብር 334,910.15 ከአንድ አመት በላይ ፤
- በየሂሳብ መደብ 4274 ከSocio ብር 151,169.58 ከአንድ ዓመት በላይ

በአጠቃላይ በድምሩ ብር 8,916,162.69 ውዝፍ የፕሮጀክት ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፤

8. <u>በወቅቱ ለባለመብቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ</u>፣

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8/5 ፊደል ሀ መሠረት ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸው የሚያረጋግጥ በቂ መረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት የመደበኛ እና የፕሮጀክት ሂሳብ የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፡-

<u>ከመደበኛ ሂሳብ</u>፣

በዋናው መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቶች የተጠቃለለው የሂሳብ ሪፖርት ላይ፡-

- በሂሳብ መደብ 5002(6172202) ብር 1,501,236.47
- በሂሳብ መደብ 5054 (6172106) ብር 93,651.00 ፤
- በሂሳብ መደብ 5516(6174299) ብር 497,990.39

በድምሩ ብር 2,092,877.86 ከአንድ ዓመት በላይ ለባለመብቱ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፣

<u>ከፕሮጀክት ሂሳብ</u>፣

በሂሳብ መደብ 5002 ከ Finger print ብር 379,287.95 ፤ ከ FS12 ብር 242,666.96 ፤ ከSocio ብር 702,121.81 በድምሩ ብር 1,324,076.72 ከአንድ ዓመት በላይ ለባለመብቱ ያልተከፈለ የፕሮጀክት ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፣

በኦዲት ታውቋል፡፡

9. <u>ከበጀት በላይ ጥቅም ላይ የዋለ በጀት በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል::በተጨማሪም በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት አገልግሎት

መ/ቤቱ በጀቱን የሚቆጣጠር መሆኑን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው ከ10% በላይ ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፡-

ከካፒታል በጀት ብር 143,823.08 ዝውውር ሳይደረግና በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ለሀገር ውስጥ ስልጠና ከተመደበው በጀት በላይ ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት